★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

*ዴሞክራሲያ ቅፅ* 33 *ቁ*.3 *ታኅሣሥ* 2000 *ዓ. ም*

# *የኢሕአፓ ዋና ዋና ሀገራዊ ፖሊሲዎች*

*የድርጅቱ መነሻና መድረሻ መሠረት ያደረገው፥ ወደፊት ከሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ስር በሚተዳደሩ ሀገራዊ ፖሊሲዎች ላይ ነው። የፓርቲው ብሔራዊ ፖሊሲዎች የድርጅቱ ራዕይ ቀጥተኛ ነፀብራቅ ናቸው። ፓርቲው ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይበጃል ብሎ ባመነባቸው ሀገራዊ ፖሊሲዎች ላይ ቅድሚያና አፅንዖት በመስጠት በፖለቲካ ፕሮግራሙ ውስጥ አስገብቶ፥ የሚሻሻሉትንም በሂደት እያስተካከለ የትግሉ ማዕከል እንዲሆኑ አድርጎ እስከ ዛሬ ድረስ በመታገል ላይ ይገኛል።*

*እነኝህ ሀገራዊ ጠቀሜታ አላቸው ብለን የመዘገብናቸው ዋና ዋና ፖሊሲዎች በተግባር በሚተረጎሙበት ወቅት፥ የሀገራችንን ሁለንተናዊ ችግር በሂደት ይቀርፉታል ብለንም እናምናለን። የፓርቲው ብሔራዊ ፖሊሲዎች በቀጥታ የሚያተኩሩት፥ የሀገራችንን መሠረታዊ ችግሮች፥ ማለትም፥ ረሀብን፥ በሽታን፥ ድኅነትን፥ ኋላ ቀርነትን፥ ለማጥፋት በሚደረጉ እርምጃዎችና ውጤቶች ላይ ቅድሚያ መስጠት ሆኖ፥ በዘለቄታ መልኩ ደግሞ የሀገራችንንና የሕዝባችንን ብሔራዊና ዘላቂ ጥቅም ማስጠበቅ ይሆናል። ይህም ለቆምንበት ዓላማ አልፋና ኦሜጋችን ነው። ከዚህ የበለጠ ሌላ ቀዳሚይና ዳሕራይ ወይም ዋነኛና መጨረሻ ጉዳይ የለንም።*

*በራዕዩ ላይ ተመሥርተው በፓርቲው የፖለቲካ ፕሮግራም ውስጥ የተቀረፁት እነዚህ ሀገራዊ ፖሊሲዎች፥ በተግባር ሊተረጎሙ የሚችሉት፥ በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአስተማማኝ ሁኔታ ሲረጋገጥ ብቻ ነው ብለን እናምናለን። በአስተማማኝ ደረጃ ስንል፥ የሕዝብን ሙሉ ነፃነት፥ የሀገርን ሉዓላዊነትና የሕግን የበላይነት መሠረት ያደረገ*

ሕገ መንግሥት ህያው ሲሆንና የሀገሪቱም ዜጎች ያለ አንዳች ገደብ ተሳታፊ ሲሆኑ ነው ማለታችን ነው፡፡ሕገ መንግሥትን ያህል መሠረታዊ የሀገር ሰነድ ህያው ነው የሚባለው፥ ነዋሪዎቿን የሚያሳትፍ ዴሞክራሲና አንዱ ከሌላው አንድ አምሳል አንድ አካል መሆኑ የሚረጋጥበት ሁኔታም ሲኖር ነው፡፡ ይህ ክስተት ሦስት መሠረታዊ ጥቅሞች ይኖሩታል፡፡ እነዚህም፥ አንደኛ የሕዝብን ነፃነት ከማረጋገጥ አኳያ አስተማማኝ ይሆናል፡፡ ሁለተኛ አምባገነን እንዳያቆጠቁጥ ለመከላከል ይረዳል፡፡ ሦስተኛ የሀገሪቱን ዜጎች ሁሉ ያለምንም ገደብ ስለሚያሳትፍ የብሔራዊ ዕድገትን ለማስፋፋትና ለማፋጠን ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ በመሆኑም፥ አሳታፊ ዴሞክራሲ የአንድን ሀገር ሕገ መንግሥት ህያውነት ከሚያረጋግጡ መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል አንዱ መሆኑ ሊያከራክር አይችልም፡፡

ፓርቲው፥ ብሔራዊ ፖሊሲዎችን በፕሮግራሙ ውስጥ የቀረፃቸው፥ ከሚከተለው የፖለቲካ መስመር ጋር እንዲጣጣሙና የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታዎችንም የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ነው፡፡ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ስናተኩር፥ ዛሬ ኢትዮጵያ በመላው ዓለም ከሚኖሩ ሕዝቦች ውስጥ በሁሉም ዓይነት የዕድገት መስፈርት ስትለካ፥ ከመጨረሻው ዕርከን ላይ እንደሆነች እናውቃለን፡፡ ሰማንያ አምስት በመቶ የሚሆነው ሕዝብ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በእርሻ ተግባር ላይ የተሰማራ ነው፡፡ የእርሻው ዘዴም በጥንታዊ አተራረስና የምርት አሰባሰብ ሂደት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ፥ አንድ ገበሬ፥ ዓመቱን ሁሉ ሲማስን ባጅቶ፥ የሚያገኘው ምርት ቤተሰቡን እንኳን ለወራት ሊመግብ የሚያስችለው አይደለም፡፡ ይህ የጥንታዊ የእርሻ ዘዴ፥ ዝንተ-ዓለሙን ከድህነትና ከረሃብ እንዳይወጣ አድርጎታል፡፡ የአንድ ገበሬ ሚስት ከጀምበር መውጣት እስከ ፀሐይ መግባት ድረስ ስትማስን ውላ የድካሟን ዋጋ ለማግኘት አትችልም፡፡ ልጆቿን አጥግባ፥ ቤተሰቧን አልብሳ፥ ጤናቸውን ጠብቃ፥ እረፍት አግኝታ፥ የመንፈስና የአዕምሮ ደስታን ለማግኘት የታደለች አይደለችም፡፡ የተሟላ የጤና አገልግሎት፤ የተጣራ ውሃ፥ ትምህርት ቤት፤ የመገናኛና የመጓጓዣ አገልግሎት ታገኛለች ተብሎ አይታሰብም፡፡ ባሏም ከእርሻው ያገኛትን አነስተኛ ሰብል ገበያ ወስዶ መሸጥ የሚያስችለው መንገድ ስለሌለው፥ በዚህ ረገድ ምን ያህል የፀና ችግር እንዳለበት ሊረዳው የሚችለው ራሱ ገበሬው አርሶ አደሩ ብቻ ነው፡፡ በበርካታ ሚሊዮን የሚቆጠረው የገጠር ነዋሪ ሕዝብ የሚኖርበት አሳዛኝ ሁኔታ በቅርብ ሁኖ ለተመለከተው፤ ሀገራችን በሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ውስጥ ገብታለች ብሎ ለማመን ይቸግረዋል፡፡

የትኩረታችንና የጭንቀታችንን ዒላማ ቅድሚያ የሰጠነው በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ለሚኖረው ጎስቋላ ሕዝባችን አሳዛኝ የኑሮ ሁኔታ ቢሆንም፤ አብዛኛው የከተማ ነዋሪው ወገናችንም፥ የሚመራው ሕይወት፥ ከብዙ አንፃር ሲታይ ከገጠሩ ኢትዮጵያዊ ሕይወት የተሻለ አይደለም፡፡ ምናልባት በከተማው ብልጭልጭና ሰው-ሰራሽ የሆኑትን ቁሳቁሶች እያየ የዘወትር የኑሮ ችግሩን ትኩረት አቅጣጫ ለመለወጥ የሚያስችለውን ጊዜያዊ እፎይታ ለማግኘት ይረዳው እንደሁ እንጅ፥ በመሠረቱ በኑሮ ደረጃ ያለው ልዩነት እምብዛም ነው፡፡ በጣም ጥቂት የሆኑትን የናጠጡ ሀብታሞችን የተንደላቀቀ ኑሮ እያየ የበይ ተመልካች ከመሆን በቀር፥ ከገጠሩ ደሃ ገበሬ የተለየ ሕይወት ይመራል አይባልም፡፡ የኢትዮጵያ ከተሞች ሕይወት ለብዙ ዜጎች የምድር ገሀነም ነው፡፡ የሥራ አጡ ብዛት፥ የወጣት ሴቶች በሚያሳዝንና በሚያዋርድ ተግባር መሰማራት፥ የበርካታ ወጣቶች በአደንዛዥ ዕፅ ልምድ መበከልና በልዩ ልዩ ወንጀል ድርጊቶች መሰማራትና የኑሮ ውድነት ሰማይ-ጠቀስ መሆን፥ ሁሉ ሲደመር፥ ለአብዛኛው ዜጋ የከተማ ነዋሪዎችን ሕይወት ምድራዊ ሲዖል አድርጎታል፡፡

ይህ ሀገሪቱ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ በኩል የቱን ያህል ቀውስ እንደገባች የሚጠቁም ቢሆንም፥ በፖለቲካው ረድፍ ደግሞ የቀውሱ ጥልቀትና ስፋት ብቻ ሳይሆን፥ ውስብስብነቱ እጅግ የተጥመለመለና የመፍትሔው ውልም የተደነባበረ መሆኑን ሁሉም ዜጋ ተረድቶታል፡፡ ሀገራችን ዛሬ በአንድ አናሳ ብሔር የተደራጀና የታጠቀ ቡድን የውጭ ኃይል ድጋፍ አግኝቶ መላውን የሀገሪቱ ዜጎች በአምባገነንነት የሚገዛት ምድር ሆናለች፡፡ ዜጎች በሀገራቸው በሰላምና በነፃነት፥ በተረጋጋ መንፈስና አዕምሮ ሊኖሩባት አልቻሉም፡፡ በሆነው

መንገድ ሀገሩን ለቅቆ መሰደድ ተቀዳሚ ፍላጎቱ የሆነበት ዜጋ ቁጥር ትንሽ አይደለም:: ቁጥሩን በትክክል ለማወቅ ያልተቻለ ዜጋ እንበለ ፍርድ በተለያዩ ማጎሪያዎች እየተሰቃየ ይገኛል:: በየቤቱ እየታፈነ መዳረሻው የማይታወቀውን ሕዝብ ቤቱ ይቁጠረው ከማለት በስተቀር፥ ትክክለኛውን አሃዝ መናገር የሚቻል አይደለም::

በአንዳንድ የሀገሪቱ የፖለቲካ ታዛቢዎችና ተንታኞች አመለካከት፥ የወያኔን አገዛዝ ከሂትለሩ አገዛዝ ጋር ያነፃፅሩታል:: ሁለቱም በዘር ላይ የተመሠረተ ሥርዓት ያራምዳሉ:: የስለላ መዋቅራቸውና የመጨቆኛ ተቋማታቸው፥ የተወርዋሪ ጨፍጫፊዎቻቸውና የማሰቃያ ዘዴያቸው ከሞላ ጎደል ተቀራራቢዎች ናቸው:: አንድ የሚለያቸው መሠረተዊ ነገር ቢኖር፥ ሂትለር " ከሁሉ በፊት ጀርመን! " ማለቱና ወያኔዎቹ ደግሞ፥ "ለእኛ ያልሆነች ሀገር ትበጣጠስ !" ማለታቸው ብቻ ነው:: ሂትለር ከጀርመን ዳር ድንበር አልፎ ተርፎ ዓለምን ለመውረር ሲያብድ፥ ወያኔዎቹ ደግሞ ከተነሱበት ክፍለ ሀገር ወጥተው አጎራባች ክፍለ ሀገሮችን እየወረሩ የትግራይን የቆዳ ስፋት መለጠጣቸው፥ ሁለቱንም ዘረኞች በተፃራሪ ንፅፅር ያስቀምጣቸዋል:: ሂትለር፥ ጀርመን ወይም ሞት ሲል፥ ወያኔ ደግሞ ትግራይ ወይም ሞት ብሎ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ፥ ቋሚና ተቀዳሚ ጠላት መሆኑን በተግባር አስረግጧል:: ሂትለር ከጀርመን ሕዝብ ሆ! የሚልለት ወገን እንደነበረ ሁሉ ለወያኔም ይህንን የሚያረግ ያካባቢው ተወላጅ የለም ማለት ባይቻልም የወያኔ ግብሩና ሥራው ግን ደጋግመን እንደገለፅነው ከትግራይ ሕዝብ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም:: በግብረ ጥፉነት መቀጠሉ የኋላ የኋላውን መዘዝ ግን ወያኔ እስከዛሬም አልተረዳውም:: በዕርግጥም የሀገራችን ሁኔታ በግድም ሆነ በውድ መለወጥ ይኖርበታል!

ይህ የሀገራችንን ሁኔታ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየውን ሃቅ ለመለወጥ ያስችለናል ብለን የመረጥነው የፖለቲካ መስመር፤ አማራጭ፤ ርዕዮተ ዓለም ሶሻል ዲሞክራሲ ነው ብለን ከዚህ በፊትም ገልፀናል:: ሶሻል ዲሞክራሲ ስንል፥ ይህ ህበረተሰባዊና ሰፊውን ሕዝብ አቀፍ ለሀገራችን ዕድገት በጣምራ መልክና ሂደት ጥቅም ያስገኛል ማለታችን ነው:: ይህ የጣምራ ሂደት ሁሉንም የሀገራችንን ኅብረተስብ ፍላጎት ያስተናግዳል ለማለት ይቻላል:: ይህም ለምንታገልበትና ለምንሰዋለት ብሔራዊ ራዕይና ዓላማ፥ ብሎም ለሀገራችን ብሔራዊ ጥቅም ምላሽ ሊሰጥልን ይችላል ከሚል ዕምነት የመነጨ ነው:: በሶሻል ዲሞክራሲ የፖለቲካ መመሪያችን ዙሪያ የደሀ ገበሬውን፥ የሠራተኛውን፥ የከተማ ነዋሪውን ጎስቋላ ኑሮን፥ ጧሪ የሌላቸውን አዛውንትን፥ ዕጓለ ምውታንን፥ የነዳያኑን የአካለ-ስንኩላኑን ወዘተረፈ ሁኔታ ለማስተናገድና ምላሽ ለመስጠት የሚችል ፕሮግራም፤ አማራጭ መስመር እንደሚሆን እንመኛለን:: በሌላ በኩል ደግሞ፤ የዲሞክራሲን መሠረታዊ ዓላማና ግብ፥ አሰራርና ሂደት ፍልስፍናና ድርጊት መሠረት ያደረገ የመንግሥት አመሰራረትና አካሄድን አንግቦ የሚጓዝ እንዲሆን እንሻለን፥እንፈልጋለን፥ እንታገላለንም::

ታዲያ ይህ ከላይ የተዘረዘረው የሶሻል ዴሞክራሲ ፖለቲካ አቋም ጠቅለል ብሎ ሲነገር፥ ሁሉንም የሀገራችንን የኅብረተሰብ ክፍል፥ ዕድሜ ፥ ፆታ፥ መደብ፥ ከተማ-ገጠር፥ ሃይማኖት፥ ዘር፥ ደካማ- ብርቱ፥ ሠራተኛ- አሠሪ ወዘተ ሳይለይ፥ ሁሉንም የሀገሪቱ ዜጎች፥ ያለአደልዎ በአንድ ብሔራዊ ሕገ መንግሥት ጥላ ስር የሚያስተናግድና ለሀገራዊ ዕድገት ሁሉን የሚያሳትፍ የመንግሥት መመሪያ ይሆናል:: በእኛ ዕምነት፥ ስለ ማንኛውም ብሔራዊ ፕሮግራም፥ ወይም ሀገራዊ ፖሊሲዎችም ሆነ የልማት ዕቅዶች፥ ከማሰባችን በፊት፥ በዋናነት መሠረት ሊጣልለት የሚገባው የሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ጉዳይ መሆን አለበት እንላለን:: በሕዝብ ተሳትፎና ውሳኔ፥ላይ የተመሠረተና ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች ያፀደቁት ሕግ መንግሥት መኖር፥ ከሁሉም በፊት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነውናም፥ ማንም አስተዋይ ሀገር ወዳድ ዜጋ የሚያምንበት ለመሆኑ ልንጠራጠር አንችልም:: ለዚህም ነው፥ ስለ ዴሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ጉዳይ የተለየ ትኩረትና አፅንዖት ሊሰጠው ይገባል ብለን የትግላችን የቅድሚያ ጥያቄና ተልዕኮ ያደረግነው::

ከወያኔ ጋር ካሉን መሠረታዊ ልዩነቶች መካከል ዋነኛው፥ የሕገ መንግሥት ጉዳይ ለመሆኑ ሁሉም ዜጋ የሚያውቀው ስለሆነ ወደ ዝርዝር ነጥቦች መሄድ የሚያስፈልገን ሆኖ አላገኘነውም። ማንም ድርጅት ይሁን ነፃ አውጭ ግንባር ነኝ ባይ ሁሉ፥ በኃይል ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ፥ የራሱን ውስንና ጠባብ የፖለቲካ ፕሮግራም በሰው ሰራሽ ሂደትና ዘዴ፥ ልክ እንደ ወያኔ፥ የሀገሪቱ ሕገ መንግሥት አስመስሎ ሊያቀርብ አይችልም። አይፈቀድለትምም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በተፈራራቂ አምባገነን መሪዎች የተገነዘበው መራራ ተመክሮ ቢኖር፥ የዴሞክራሲ መብቶች ታፍነው፥ ሕዝቡ ያልተሳተፈበትና ይሁንታውንም ሊሰጥ ባልቻለበት ሁኔታ እንኳን "ሕገ መንግሥት" ተብሎ በመቁንን መቸሩ ነው። የዚህ ቀጥተኛ ውጤት ደግሞ፥ ሀገሪቱ አሁን ያለችበትን፥ የወደቀችበትን ሁለንተናዊ ችግርና ጥፋት አስከትሏል። የሰው ልጅ ነፃነትና መብቶች በሌሎች ምፅዋትና ችሮታ፥ በጎ ፈቃድና ሀዘኔታ የሚሰጥ አይደለም። የሰው ልጅ ነፃነትና መብት፥ ሰው በመሆኑ ብቻ፥ በሰብዓዊ ተፈጥሮው ያገኛቸው የማይደፈሩና የማይገሰሱ፥ የማይለወጡና የማይሸረፉ ናቸው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፥ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን በርጥባን ሊያገኝ አይፈልግም። አኩሪ ታሪክ ላለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይህ ድርጊት ውርደት ነው። ይህ የወያኔ ሥርዓት የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊያዋርድና ሊበድል ቆርጦ መነሳቱን ደግሞ በእሮሮ መገንዘብ ከተገደደን ዓመታት አልፈዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹ፥ በተፈራራቂ አምባገነን ሥርዓት ሲረገጡ እንደቆዩ ሁሉ፥ አሁንም በዚያው ታፍነው እንደቀጠሉ ናቸው። ኢትዮጵያ ሀገራችን ከዚህ የብሄራዊ ችግር አዙሪት ለአንዴና ለመጨረሻ መላቀቅ አለባት። ኢሕአፓ፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይጠቅማሉ ብሎ ያመነባቸውን ሀገራዊ ፖሊሲዎቹን፥ በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ውስጥ እንዲካተቱለት የሚታገለው፥ ኢትዮጵያ ከዘረኞች አምባገነን ሥርዓት ከተላቀቀች በኋላ፥ በሕዝቧ ቆራጥ ተጋድሎ በምታገኘው ሰላምና መረጋጋት መሠረት፥ ዲሞክራሲያዊ ሕይወት መምራት ስትጀምር ነው። ለዚህ ሁኔታ መመቻቸት መታገል ብቻ ሳይሆን፥ ለመጭው ብሩኅ ተስፋ ተዘጋጅቶ መቆየትም አስፈላጊ እንደሆነ እናምናለን። የፓርቲውን ዋና ዋና ሀገራዊ ፖሊሲዎች ለምንታገልለት ሕዝብ ዳግም ማሳወቅም የትግል ግዴታችን እንደመሆኑ፥ ይህንን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

የኢሕአፓ ፖሊሲዎች ጠቅለል ባለ መልኩና አቢይና ዋና በሆኑ ይዞታዎች ሲቀርቡ በሚከተሉት ቅርፅና ይዘት ሊያካተቱ ይችላሉ።

<u>የዓላማችን መቅድም የሆነው፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሉዓላዊነትና የሥልጣን ምንጭነት በሕግ የሚረጋገጥበት፥ በዜጎች እኩልነት ላይ የተመሠረተ፥ የሕዝብና የሀገር አንድነት የሚጠበቅበት፥ የዕምነት፥ የኃሳብና የኅሊና ነፃነት የሚከበርበት፥ በሕዝብ ነፃና ርቱዓዊ ምርጫ የሚቋቋም ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መመሥረት ይሆናል።</u>

ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚያስችሉት የሕዝብ የማዕዘን ድንጋዮች፥ መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዋዊ መብቶች መረጋገጥ ናቸው። የዓላማችን መቅድም የሆነውን የወደፊቷ ኢትዮጵያን ለማየትም መሠረቱ ይህ ነው።

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው፥ ሀገራችን በድኅነት የመጨረሻውን ደረጃ መያዟን ከተገነዘብን ዘንዳ፥ ኢትዮጵያ ቅድሚያ ልትሰጠው የሚገባት ብሔራዊ ኢኮኖሚዋን መገንባት እንደ አጣዳፊና አንገብጋቢ ጉዳይ ሊቆጠር ይገባል። በመሆኑም፥ የድኅነታችንን ምክንያቶች በሂደት ለመቅረፍ፥ <u>ብሔራዊ ብልጽግናን መሠረት ያደረገ የሀገሪቱንና የሕዝቧን ጥቅም ያካተተና ቅድሚያ የሰጠ፥ በገበያ ኢኮኖሚ መርኅ ላይ የተመሠረተ ብሔራዊ ኢኮኖሚ</u>

<u>መገንባትና የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል ብሔራዊ ፖሊሲያችን ነው ፡፡</u> ሰማንያ አምስት በመቶ የሀገራችን ሕዝብ ኑሮ የተመሠረተው በግብርና ላይ በመሆኑ፥ በዋናነት የመሬቱን ይዞታ መለወጥ፣ መሬት ለአራሹ መሆኑን ማረጋገጥና በእርሻ ላይ የተመሠረተ እንዱስትሪ (አግሮ-እንዱስትሪ) ማስፋፋት ተመጣጣኝ የሆነ የዕድገት ዕርምጃ ማምጣት ፍላጎታችንና ተስፋችን ነው፡፡ ያልተነካው የሀገራችን ድልብ የተፈጥሮ ሀብትና የከርሰ ምድር ማዕድናት ለሕዝብ ጥቅም የሚሆኑበትን ሁሉ ማበረታታት፥ ብሔራዊ ኢኮኖሚን ከመገንባት አንፃር ዋነኛውን ክፍል ሊይዝ ይገባል፡፡

ነፃ የሀገር ውስጥና የውጭ የንግድ እንቅስቃሴ፥ የባንክ፥ የፋይናንስ፥ የመድኅን (ኢንሹራንስ) መስፋፋት በሀገራችን የኢኮኖሚ ፖሊሲ ሕግና ሥርዓት እንዲከናወን ማድረግ፥ ማንም ክፍል ወይም ባለሥልጣን ያላግባብ እንዳይጠቀምበት ለማድረግ ወሳኝ ነው እንላለን፡፡ በነፃ ገበያ ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ፖሊሲ የሕዝቡን ሙሉ ተሳትፎ የሚያስተናግድ እስከሆነ ድረስ፥ ከድህነታችን ለመላቀቅ በሚደረገው ጥረት ዓይነተኛ ሚና እንደሚጫወት እንረዳለን፡፡ ሠርቶ አደሩን ሕዝብ ግን ለጭፍን ብዝበዛ አሳልፎ የሚሰጥ ሥርዓት መስፈኑን ኢሕአፓ አይደግፍም፡፡

<u>የሠለጠነውን የሰው ጉልበት፥ ገበሬውና ከሠራተኛው ኃይል እንዲሁም፥ ከሀገሪቱ የተፈጥሮ ሃብት ጋር አስተባብሮ የዕድገት ጎዳና ለመቀየስ፥ በሕግ ላይ የተመሠረተ ነፃ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መዘርጋት፥ ሀገራችንን ከዓለም ተመጽዋችነት ነፃ እንደሚያደርጋት የጋለ ተስፋ ብቻ ሳይሆን፥ በራሳችን መተማመንን ያረጋግጥልናል እንላለን፡፡</u>

ከሀገራዊ ኢኮኖሚ ፖሊሲያችን ጋር ተለይቶ የማይታየውና አንዱ ከሌላው ጋር ተደጋጋፊ ነው ለማለት የሚቻለው፥ ብሎም፥ ለሀገር ዕድገትና ብልፅግና መሠረታዊ ሚና የሚጫወተው፥ የሀገራችንን የትምህርት ሥርዓት (ፖሊሲ) ለብሔራዊ ጥቅም እንዲውል ማድረግ ነው፡፡ ትምህርት፥ ከሀገሪቷና ከሕዝቧ ታሪክ፥ ባህልና ልምድ እንዲሁም ፍላጎትና ጥቅም ጋር ተቀናጅቶ የሚራመድበትን ፖሊሲ መንደፍ አስፈላጊ ነው፡፡ ትምህርት ከምርት ሥራ እንዳይነጠል ሆኖ፥ መሃይምነትን ማጥፋትና ዕድሚያቸው ለትምህርት የደረሱ የሀገሪቱ ህፃናት የትምህርት ዕድል በነፃ ማግኘት የዜግነት መብታቸው ብቻ ሳይሆን፥ የመንግሥት ግዴታም ጭምር መሆኑን በሀገሪቱ ሕግ እንዲደነገግ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

በድኅነት መቆራመዳችንና ከዓለም ሥልጣኔ ወደ ኋላ መቅረታችን ምክንያት ከሆኑት ዋናዎቹ፥ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ጥበብ በሀገራችን አለመስፋፋት ነው፡፡ የኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ ከሚያተኩርባቸው የሥርዓተ ትምህርት ይዘት ውስጥ፥ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መካተት ወሳኝነት አለው፡፡ ጥናትና ምርምር በሀገራችን ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ ሁነኛ ቦታ እንዲሰጠው እንፈልጋለን፡፡ የተማረ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ሀገራችን የልማትና ዕድገት መሠረት ለመሆኑ ለሕዝባችን ለማስረዳት አንቃጣም፡፡ ዕድሉ ተነፍጎት ነው እንጅ፥ የትምህርትን ጠቀሜታ ልጆቹን በላቡ ዋጋ ከአስተማረው ሕዝብ የበለጠ የሚረዳው የለም፡፡ መቸም የሀገራችን ሁለንተናዊና ሥር የሰደዱ ችግሮችን ዘርዝሮ ለመጨረስ ቢያስቸግርም፥ ለተለያዩ በሽታዎች ሰለባ የሆነው ሕዝባችን ያለበትን ሥር የሰደደ የጤና ችግር ግን እንዲሁ በአርምሞ የሚታለፍ እንዳልሆነ እንገነዘባለን፡፡ በሀገራችን ሥር የሰደዱ በሽታዎችንና ተውሳኮችን ለመዘርዝር በሙያው የሠለጠኑ ሊቃውንት የሥራ ድርሻ በመሆኑ፣ ያንን ለመመዝገብ አንቃጣም፡፡ በቀላሉ ሊወገዱ ከሚችሉት አፍለኛ ተውሳኮች ጀምሮ፥ ሥር እስከሰደዱትና የገነኑ በሽታዎች ምክንያት የሚሰቃየውን ሕዝብ ከህመም ለማላቀቅ፥ መሠረታዊ የጤና ፖሊሲ አውጥቶ በየፈርጁ ተግባራዊ ማድረግ አማራጭ የሌለው ተግባር እንደሆነ ግን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ተግባራዊ ለማድረግ ከሚያስችሉት አንዱና መሠረቱ፥ ለሕዝብ የሚያገለግል የጤና ሥርዓት ማቋቋም ነው፡፡ የሕዝቡን ጤና ለመጠበቅ ብሔራዊ የጤና ጥበቃ ፖሊሲ መሥርቶ፥ ለመላው የሀገሪቱ ዜጎች

የሚዳረስ የጤና ፕሮግራም መዘርጋት የአንድ መንግሥት ተቀዳሚ ተግባሩና ግዴታው እንደሚሆን የሚያከራክር አይሆንም፡፡ የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በሚፈቅደው ሂደት፥ የጤና ተቋማትን በገጠርና በከተማ በሚገባ ማስፋፋት፥ በሽታዎቹን ለመቆጣጠርና በሂደትም ለማጥፋት፥ የመጀመሪያ ርምጃ ነው፡፡ ጤናው ያልተጠበቀለት ዜጋ ከድኅነትና ከኋላቀርነት ሊላቀቅ እንደማይችል መዘርዘር የሚያስፈልገን አይመስለንም፡፡ የኢትዮጵያ ሀገራችን ዓይነተኛ ብሔራዊ ኃብቷ ዜጎቿ እንደመሆናቸው፥ የዜጎቿን ጤንነትና ደኅንነት መጠበቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ሆኖ ሳለ፥ የወያኔ አገዛዝ ተቋሞችን በማፍረስ እኩይ ተግባር መሰማራቱ የታየ ነው፡፡

የሀገር ኃብት ጉዳይ ከተነሳ፥ ከሕዝቧ ቀጥሎ የኢትዮጵያ ሕልውና ሊመሠረት የቻለው፥ በተፈጥሮ ሀብቷ ላይ መሆኑ ገሃድ ነው፡፡ በመሆኑም የተፈጥሮ ኃብትንና የአካባቢን ደኅንነትን መንከባከብ በብሔራዊ ፖሊሲ ደረጃ የሚታይ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ወንዞች፥ ሀይቆች፥ ኩሬዎች፥ ፋፋቴዎችና በውስጣቸው የሚኖሩ ተንቀሳቃሾች፥ አፈሩና አየሩ፥ የዱር አራዊትና እንስሳቱ፥ አዕዋፍ፥ ደኖች፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ኃብት ንብረቶቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነኝህን ብሔራዊ ኃብቶች ተንከባክቦ መያዝ፥ የዜጎችና የመንግሥት ኃላፊነትና ግዴታ ሊሆን ይገባል፡፡ የዓየር ብክለት፥ የአፈር መሸርሸር፥ የደኖች መመንጠር፥ የአራዊት መጨፍጨፍ፥ የአዕዋፍና ዱር አራዊት መሰደድ፥ የጫካዎች መቃጠልን ሁሉ፥ ለመከላከል የሚያስችል ብሔራዊ ፖሊሲ አውጥቶ በተገቢው መንገድ ተግባራዊ እንዲሆን እንፈልጋለን፡፡ የመለስ ቡድን ግን ገና ጫካ ሸፍቶ ሳለ ጀምሮ የሀገርን የተፈጥሮ ሀብት ሲያጠፋና ለባዕድ ሲሸጥ የከረመ ደንታ ቢስ አገዛዝ ነው፡፡

ከጥንት ጊዜ ጀምሮ፥ የሀገሩን ነፃነት፥ ሉዓላዊነት፥ ዳር ድንበርና የራሱንም አንድነት ሲያስከብር የኖረው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደነበር በታሪክ የተመዘገበ ለመሆኑ፥ ከወያኔ በስተቀር ሁሉም ዜጋ የሚያውቀው ነው፡፡ ከዚህ ታሪካዊ ሐቅ ተነስተን፥ የሀገራችን ብሔራዊ የመከላካያ ኃይል ፖለሲ፥ በጠቅላላው የሀገሪቱን ዜጎች ተሳትፎና ጥቅም፥ ሥልጣንና ይሁንታን መሠረት ያደረገ ብሔራዊ የመከላካያ ሠራዊት መገንባት፥ ለወደፊቷ ኢትዮጵያ የነፃነቷ ዋስትና መሆኑ ዕሙን ነው፡፡ ዛሬ የሀገር መከላከያ ሳይሆን፥ የወያኔ ሥልጣን መጠበቂያና መከላከያ እንዲሆን ታስቦ፥ በአንድ ብሔረሰብ የበላይነት ስር የተቋቋመ ሠራዊት መኖሩ ሊካድ የሚችል አይደለም፡፡

እኛ፥ የሀገር መከላካያ ሠራዊት ስንል፣ በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት መሠረት፥ ተጠያቂነቱና ታዛዥነቱ በሕግ ለተቋቋመ መንግሥት ሆኖ፥ የሀገሪቱን ነፃነትና የግዛት አንድነት ለመጠበቅ የሚችል በሙያተኝነት የሠለጠነ የመከላከያ ሠራዊት ማቋቋም፥ የሀገሪቱ የመከላካያ ፖሊሲ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህ ብሔራዊ የመከላካያ ሠራዊት፥ ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ/ዊት ያላገለለ፥ በሕግ የተደነገጉትን መስፈርቶች በሚያሟላ ሂደት የተመለመለ፥ የሠለጠነና የታጠቀ ጦር ኃይል ይሆናል ማለታችን ነው፡፡ ታማኝነቱና አገልግሎቱ በቀጥታ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሆኖ፥ ታዛዥነቱ ደግሞ በኢትዮጵያ ሕዝብ ለተመረጠ ሕጋዊ መንግሥት ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች አባላት፥ የፖሊስ ሠራዊትም ሆነ፥ ሌሎች የመለዮ ለባሾች አባላት በሀገሪቱ የፖለቲካ ድርጅቶች አባሎች ሊሆኑ አይገባቸውም፡፡ ምንም ቢሆን በሀገራችን ግዛት የውጭ ሀገር ጦር ኃይሎች ሊሰፍሩ አይፈቀድላቸውም፡፡ የመከላካያ ሠራዊት አባላት፥ ቀጥታ ተጠያቂነታቸውም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንጅ፥ ለተለየ ብሔር ወይም የፖለቲካ ቡድን ፈፅሞ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህ ድርጊት ከወያኔ ክስመት ጋር የሚያከትም ይሆናል፡፡ ሀገራችንም የማንኛውም ሀገር የጦር ጥገኛ አትሆንም፡፡ የብሔራዊ መከላከያ ፖሊሲያችን መሠረቱ፥ ዓላማውና ግቡ፥ የሀገራችንን ብሔራዊ ነፃነትና ክብር፥ የግዛት አንድነትና ዳር ድንበሯን ማስከበርና መጠበቅ ነው፡፡

የሀገራችን የውጭ ፖሊሲ በገለልተኛነትና ሠላምን በመፈለግ ላይ የተመሠረተ መሆኑ፥ ለሉዓላዊነታችንና ለነፃነታችን ዋስትና ይኖረዋል ብለን እናምናለን፡፡ የውጭ ጉዳይ መርሆአችን፥ የኢትዮጵያን ብሔራዊና ዘላቂ ጥቅሞችን በማስቀደምና በመጠበቅ ላይ

የተመሠረተ ሆኖ፥ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የአፍሪካ ኅብረት ያፀደቋቸውን ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ደንቦችንና ስምምነቶችን ማክበር ተገቢ ይሆናል። ከማንኛውም ሀገር ጋር በሠላምና በመተባበር፥ በመከባበርና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት መመሥረት፥ የውጭ ፖሊሲያችን የማዕዘን ዋልታችን ይሆናል። አሉታዊ ገለልተኝነት ፖሊሲን በማስመር፥ ከማናቸውም የዓለም ሀገሮች ጋር የሰላም፥ የባህል፥ የንግድ፥ የትምህርት፥ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ወዘተ... ስምምነቶች ማድረግና የሀገራችንን ሀገራዊ ጥቅም የማስፋፋት ነፃነታችን የተጠበቀ ይሆናል። ከጎረቤትና አካባቢ ሀገሮች ጋር በሰላም አብሮ የመኖር ፖሊሲያችን ህያው ነው። ኢትዮጵያ በማንም ሀገር የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ለመግባት እንደማትሻ ሁሉ፥ ማንም ሀገር ቢሆን በራሷ የውስጥና የውጭ ጉዳይ እንዲገባ አትሻም፥ አትፈቅድምም። ይህም ዛሬ ሰፍኖ ያለውን የወያኔ ተንበርካኪ መሪዎች ባህርይና ድርጊት የሚፃረር ይሆናል።

የማነኛውም ሀገር የውጭ ፖሊሲ የዚያው ሀገር የውስጥ አስተዳደርና ፖሊሲ ቀጥተኛ ነፀብራቅና ውጤት ነው ብለን ስለምናምን፥ የኢትዮጵያ ሀገራችን የውጭ ፖሊሲ በዓለም አቀፍ ደረጃ አክብሮትና ተቀባይነት እንዲያገኝ ከተፈለገ፥ የውስጥ ፖሊሲያችንን በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ግዴታችን ይሆናል። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ መንግሥት ማቋቋም፥ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የማዕዘን ድንጋይ እንደሚሆን የምናምንበት ነው። በሀገራችን ውስጥ፥ የዓለም አቀፍ ሰብዓዊ መብቶችን አዋጆች፥ ሕግና ደንቦች እንዲሁም ሌሎች የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ማክበር-ማስከበር፥ ለምናራምደው የውጭ ፖሊሲ፥ ከበሬታ፥ ተአማኒነትና ተቀባይነትን ያተርፍልናል ብለን ስለምንገምት፥ የሀገራችን ዜጎች በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መብታቸውን መጎናፀፋቸው አማራጭ አይኖረውም።

ለሃያ አንደኛው ምዕተ ዓመት ለሀገራችን ያለን ራዕይ በብሩኅ ተስፋ ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ፥ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የምንመኝለትን ሀገራዊ ፖሊሲዎችና የዲሞክራሲ ሥርዓት መስፈን፥ የትግላችን መሰረት ነው። ሀገራችን በብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ፀጋ የተጎናፀፈች መሆኗ፥ ለብልፅግናዋ፥ ለጥንካሬዋ፥ ለነፃነቷና ለዕድገቷ መሠረት ነው ብለን አጥበቀን እናምናለን። በመሆኑም፥ በዜጎች እኩልነት ላይ የተመሠረተ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት፥ የማይገፈፍ፥ የማይሻር፥ የማይናወጥና ለድርድርም የማይቀርብ የሀገራችን ህልውና መሠረቱ፥ ማዕዘኑ፥ ዋልታና ማገሩ፥ ጣሪያውና ጉልላቱ ነው። ኢትዮጵያ፥ የወያኔ መሪዎች እንደሚሉት፥ የመቶ ዓመት ረጋ-ሠራሽ ሀገር ሳትሆን፥ የጥንታዊ ሥልጣኔ ባለቤት የነበረች፥ ነፃነቷንና የራሷን ባህል፥ ታሪክ፥ ፊደል፥ ማንነትና ሰብዕና ጠብቃ የቆየች አፍሪካዊት ሀገር ነች። ይህም ማንነቷ ዕውን ሊሆን የበቃው፥ ተዋዶ፥ ተስማምቶ ተባብሮና ተከባብሮ ለዘመናት በአንድ ላይ በኖረው ታላቅ ሕዝቧ ተጋድሎና ማንነት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ፥ ጠባብ ብሔረተኞች እንደሚሉት የ "ትምክህተኞች" ተረት- ተረት ሳይሆን፥ በአያሌ ዘመናት ሂደት በታላላቅ የታሪክ ደራሲያን ዜና መዋዕል የተመዘገበ፥ በጥንታዊ ቅርጾቿና ታላላቅ ሃውልቶቿ ህያውነት የተረጋገጠ፥ በአበይት የሃይማኖት መጽሐፍት ማኅተም የታተመ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለታሪኩ፥ ለነፃነቱ፥ ለባህሉ ፥ ለታሪኩና ለሀገሩ ቀናዒ በመሆኑ፥ ያለፈው ትውልድ እስካለንበት ዘመን ድረስ ይህችን ሀገር አቆይቶ፥ ለዛሬው ትውልድ አስረክቦ አልፏል።

የኢሕአፓ አካላት-አባላት ከመጀመሪያውም በፓርቲው ሥር ተሰባስበው ትግል የጀመሩትና ለአለፉት ሠላሳ አምስት ዓመታት ታላቅ መሥዋዕት እየከፈሉ በፅናት የቆዩበት ዓይነተኛው አብነት፥ ይህችን ታሪካዊ ሀገር፥ ለመገንባትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማብቃት ነበር። አሁንም ቢሆን ይህ በደምና አፅማቸው የተገነባውን ቃል ኪዳን አክብሮ ኢትዮጵያን ከዘረኞች ጥፋት አድኖ ታላቂቱን ሀገር ከመገንባት በቀር ሌላ የግልም ይሁን የትግል አጀንዳ የላቸውም።

የፓርቲው ሀገራዊ ፖሊሲዎቹም የተመሠረቱት በዚህ ብሔራዊ ራዕይና ቃልኪዳን ላይ ነው። የኢሕአፓ ቆራጥ አባላት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጎን በመሰለፍ፥ ሀገራቸውን ከጥፋት ለማዳን የሚጠበቅባቸውን መሥዋዕት ለመክፈልና የወያኔን መሪዎች አስወግዶ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት እየታገሉ ናቸውና ከግባቸው ሊያግዳቸው የሚችል አንዳችም ምድራዊ ኃይል እንደማይኖር በዕርግጠኝነት ተማምነው ትግላቸውን ቀጥለዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አቸናፊነት እርግጠኛ ነው!!
በተባባረ ትግል ሀገራችንን እናድን!!
እናቸንፋለን!!!!